**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚችሎት**

የሰ.መ.ቁ. 213738
ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች:- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች:- 1. አቶ ንጉሴ ወ/ማሪያም
2. አቶ ጌታቸው ወ/ማሪያም
3. አቶ ፀጋዬ ወ/ማሪያም
} ጠበቃ ገ/ክርስቶስ ገ/ማርያም ቀረቡ

ተጠሪዎች:- 1. ወ/ሮ አሰለፈች ንጋቱ

2. አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 188603 ታህሳስ 7 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 270002 ሰኔ 3 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት እና ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች ተከሳሾች፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌለው የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ቤቶች አስተዳደር ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን

*ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 511 ቤት ግቢ በስተጀርባ ከደቡብ በኩል የተወረሰ እና 1ኛ ተጠሪ የምትኖርበት የቤ.ቁ 510 የሆነ ቤት አለ፣ አመልካቾች እና 1ኛ ተጠሪ  በጋራ የምንጠቀምበትን መጸዳጃ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለአመልካቾች ፈቃድ በማፍረስ ሰርቪስ ቤት በመስራት እንዳንጠቀምበት አድርጋለች፣ 1ኛ ተጠሪ ማንም ሳይፈቅድላት ከምንኖርበት ቤት በስተሰሜን በኩል ከአመልካቾች ቤት ግድግዳ በማስጠጋት በግምት 100 ካ.ሜ አስፋፍታ ያጠረችውን አጥር እንድታፈርስ በተደጋጋሚ ተጠይቃ ፍቃደኛ አልሆነችም፣ 2ኛ ተጠሪም ከፕላን ውጪ ያለፈቃድ የተሰራውን እንዲያፈርስልን እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪን ሕገወጥ ግንባታ አስቁሞ በሽንት ቤት የምናገኘውን አገልግሎት ወደ ነበረበት እንዲያስመልስን፣ 1ኛ ተጠሪ ወደ ይዞታችን ገብታ ያላግባብ ያጠረችውን አጥር እንድታፈርስ ጠይቀነው ለማስፈጸም ፍቃደኛ አይደለም፣ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ የተገነባውን ሰርቪስ ቤት እንድታፈርስ እና መጸዳጃ ቤቱን ወደ ነበረበት እንድትመልስ አስፋፍታ ያጠረችውን አጥር በተሰጠው የፕሮፖርሽን ካርታ መሰረት እንድታፈርስ፣ 2ኛ ተጠሪም የተሰራውን ግንባታ አስፈርሶ የጋራ መጸዳጃ  ቤት በ1ኛ ተጠሪ ወጪ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል እንዲያደረግ አጥሩንም እንዲያስፈርስ ይወሰንልን ሲሉ  ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡*

*የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት በኪራይ የያዙት የመንግስት ቤት ላይ አመልካቾች ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የላቸውም፣ አመልካቾች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33 ድንጋጌ አግባብ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው የሚያስይ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ነው፣ ስለሆነም የአመልካቾች ክስ በብይን ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡*

*ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከሰማ በኋላ አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መጸዳጃ ቤት በጋራ የመጠቀም መብት እንዳላቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፣ 1ኛ ተጠሪ የሚኖሩበት የቀበሌ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወረስ አከራካሪው መጸዳጃ  ቤት የጋራ ተብሎ ስለመጠቀሱ አልተረጋገጠም፣ ስለሆነም አመልካቾች ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት እና ይዞታው ላይ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው ያልተረጋገጠ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33 ተቀባይነት የለውም፣ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ቀሪ የተደረገ በመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ቀሪ ሆኗል፣ አመልካቾች በክሳቸው ውስጥ በአንድ ቦታ 1ኛ ተጠሪ አጥሩን በአመልካቾች ግድግዳ በማስጠጋት አስፋፍታ ሰራች ሲሉ በሌላ ቦታ ደግሞ ወደ ይዞታችን ገብታ አላግባብ አጥራለች የሚል እርስ በእርሱ የሚጋጭ እና ግልጽነት የጎደለው ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 231 መሰረት የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎ 1ኛ ተጠሪ ያጠሩት አጥር የአመልካቾችን የይዞታ መብት በሚጋፋ መልኩ የታጠረ እንደሆነ ክስ ማቅረብ ይችላሉ፣ የአመልካቾች ክስ ከፕላኑ ጋር የሚያያዝ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን አለው በማለት በዚህ ረገድ ጣልቃ ገብ ያቀረበውን መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡*

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾች ይህንኑ ብይን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዟል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች ክሱን ስናቀርብ ቤቱ የተወረሰበት ቅጽ በአራዳ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር ስለሚገኝ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 145 መሰረት አስቀርቦ ሳይመለከት እንዲሁም የቆጠርናቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ያቀረብነው ማስረጃ ሳይመረመር በፍሬ ነገሩ ላይ ሳያከራክር የባለሙያ አስተያየት ባልተጠየቀበት የመከላከል እና ክስ የማስረዳት መብታችንን ተነፍገናል፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለኝም የሚል ብይን ባልሰጠበት የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ብሎ መዝገቡ የዘጋው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ሲል የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢነት የለውም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት ክሱ ግልጽ አይደለም ካለ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 91 መሰረት እንዲያሻሽል ማዘዝ እየቻለ ክሱ እርስ እርሱ ይጋጫል ብሎ ውድቅ ማድረጉ እና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 145 መሰረት እንዲቀርብ በአመልካች የተጠየቀውን ማስረጃ ሳይቀርብ ውሳኔ መስጠቱን አግባብነት ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፤ አመልካቾች መጸዳጃ ቤቱ የግል ይዞታዬ ነው የሚል ክርክር አላቀረቡም፤1ኛ ተጠሪ የግንባታ ፍቃድ ከሚመለከተው አካል አግኝቼ ስለመስራቴ ተረጋግጧል፤ ቤቱ በተወረሰበት ቅጽ ላይ መጸዳጃ ቤት የመጠቀም መብት ለአመልካቾች አልተሰጠም እንጂ ተሰጥቶ ቢሆን እንኳን መንግስት የራሱ በሆነው ይዞታ ላይ የማዘዝ ስልጣን ስላለው 1ኛ ተጠሪ ብቻ ብትጠቀም ቢወስን የህግ ድጋፍ አለው፤ አመልካቾች ክስ እንዲያሻሽሉ ተደርጎ እንደ አዲስ ክርክሩ እንዲቀጥል ከማድረግ ይልቅ አዲስ ክስ አቅርበው እንዲከራከሩ በማድረግ የታለፈባቸው መብት ካላቸው መጠየቅ ስለሚችሉ ክሱ ሊሻሻል ይገባል በማለት የሰጠው ብይን ተገቢነት ያለው እና አመልካቾችም በስር ፍርድ ቤት ያላነሱት አዲስ ክርክር ነው፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ አድምጦ የሰጠው ብይን ተገቢ ነው፤ አመልካቾች መጸዳጃ ቤት የጋራ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም፤ አመልካቾች ክሳቸውን በማስረጃ አስደግፈው አላቀረቡም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጠ ብይን እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ በጋራ የሚጠቀሙበትን መጸዳጃ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለአመልካቾች ፈቃድ በማፍረስ ሰርቪስ ቤት በመስራት እንዳይጠቀሙበት ያደረጓቸው እና ማንም ሳይፈቅድላቸው ከመኖሪያ ቤታቸው በስተሰሜን በኩል የአመልካቾችን ቤት ግድግዳ በማስጠጋት አጥር ያጠሩ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪም ከፕላን ውጪ ያለፈቃድ የተሰራውን ግንባታ እንዲያፈርስ እና በመጸዳጃ ቤቱ የመጠቀም መብታቸውነ እንዲያስመልስ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ የተገነባውን ሰርቪስ ቤት አፍርሰው መጸዳጃ ቤቱን ወደ ነበረበት እንዲመልሱ እና አስፋፍተው ያጠሩትን አጥር በተሰጠው የፕሮፖርሽን ካርታ መሰረት እንዲያፈርስ፤ 2ኛ ተጠሪም የተሰራውን ግንባታ አስፈርሶ የጋራ መጸዳጃ ቤት በ1ኛ ተጠሪ ወጪ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል እንዲያደርግ እና አጥሩንም እንዲያስፈርስ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን፤ ይህንኑ ክሳቸውን ለማስረዳትም ከክሱ ጋር አያዝየው ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረቡ መሆኑን በማስረጃው ዝርዝር ተ.ቁ 1፤ 2 እና 10 ላይ የገለጿቸውን ማስረጃዎች ደግሞ ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት በትዕዛዝ አስቀርቦ እንዲመለከትላቸው የጠየቁ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ መብትና ግዴታ ምንጭ ሕግ ወይም ውል ሲሆን አንድ ከሳሽ ሌላውን ወገን በተከሳሽነት ፍርድ ቤት መክሰስ የሚያስችለው ምክንያት (cause of action) እንዲኖረው የግድ የሚል መሆኑንና ለመክሰስ የሚያስችል ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ሆኖም በአንድ ወገን ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም መኖሩ ብቻውን ውጤት የሚያመጣ ሳይሆን ከሳሹ ተጣሰብኝ ወይም ተደፈረብኝ ወይም አልተፈፀመልኝም የሚለውን ግዴታ በሌላው ወገን ላይ በሕግ ወይም በውል የተጣሰበት መሆኑን፣ ተከሳሹ መብቱ የተደፈረበት ወይም ግዴታ ያልተፈፀመለት መሆኑን፣ መብቱ በመደፈሩ ወይም ሊፈፀምለት ይገባው የነበረው ግዴታ ባለመፈፀሙ ጥቅም የቀረበት ወይም ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ እንዲሰጥለት የሚጠይቀው ዳኝነት (relief) በሕግ የተፈቀደ መሆኑን ካላሳዬ በቀር ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ስለመሆኑም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) እና 231 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መዘንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንድን ክስ የሚያቀርብ ተከራካሪ ወገን ይህንን ሊያስረዳ የሚችል ጠቋሚ ማስረጃ (Prima facie evidence) ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ከጅምሩ እንዲያስረዳ የሚጠበቀውም ክስ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ ስለመሆኑ የሚያሳይ ጠቋሚ ማስረጃ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ማስረዳት መቻል እና እንደክሱ አቀራረብ ወይም እንደተጠየቀዉ ዳኝነት ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የማስረጃ ምዘና ደረጃ ልዩነት አላቸው፡፡ ተከራካሪ የሆኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ክርክሮች ለመወሰን በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ደግሞ ተከሳሽ ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚያቀርበውን መከራከሪያ እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ፍሬነገርን አጣርተው እና ማስረጃ መዝነው ዉሳኔ መስጠት የሚጠበቅባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁ 33/2 እና 231፣ 182 እና 273 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33 እና 231 አተገባበርን አስመልክቶ በሰ.መ.ቁ 82234፣ 135639፣ 144052 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት መጸዳጃ ቤት የጋራ የተጠቃሚነት መብት ያላቸው እና የአመልካቾችን መኖሪያ ቤት ግድግዳ በማስደገፍ በ1ኛ ተጠሪ ተሰርቷል የተባለው አጥር ከለምንም ፈቃድ የተሰራ መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ክሱን ለማስረዳት የሚያስችላቸውን የተለያየ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረትም ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን በትዕዛዝ አስቀርቦ እንዲመለከትላቸው ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ክሱን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በሌላ ማስረጃ እስካልተስተባበሉ ጊዜ ድረስ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት መጸዳጃ ቤት እና አላግባብ ታጥሯል በሚሉት አጥር ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ አስረጂ ወይም ጠቋሚ ማስረጃዎች እንደሆኑ ግንዛቤ የሚወሰደበት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ክሱን ለማስረዳት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ማስረጃዎችን እስካቀረቡ እና በፍርድ ቤቱም ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው እስከጠየቁ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት ማስረጃዎቹ ከተጠየቁበት አካል እንዲቀርቡ በማድረግ፣ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ አከራካሪ የሆነው የፍሬነገር ጭብጥ ከተለየ በኋላ አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ተለይተው፣ ተመዝነው እና ከተገቢው ሕግ ጋር ተገናዝበው አመልካቾች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸው በመግለጽ ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ  ከወዲሁ አመልካቾች ከመነሻውም ቢሆን ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል አይደለም፡፡
በሌላ በኩል አመልካቾች አላግባብ በ1ኛ ተጠሪ ታጥሯል ያሉት አጥር ራሱን የቻለ ጥያቄ እንጂ ከጸዳኛ ቤቱ በጋራ የመጠቀም መብት ጋር እርሱ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም የሚያስብል አይደለም፣ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስም 1ኛ ተጠሪ አላግባብ ፈጽመውታል በሚል የተጠቀሰውን ተግባር ለማስቆም አስተዳደራዊ ግዴታውን አልተወጣም ከሚል መነሻነት የቀረበ በመሆኑ አብሮ ተጠቃሎ የሚታይ ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እንደክስ አቀራረባቸው ለማስረዳት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ከተለዩ በኋላ በእያንዳንዱ ማስረጃ ላይ ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ትንታኔ በመስጠት አመልካቾች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ለማስወሰን የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን አለመሆኑን ለይተው ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንኑ ሳያደርጉ አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት ንብረት ላይ

መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2፣ 33/3 እና 231/1/ሀ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና ኢ-ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሣኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 188603 ታሕሳስ 07 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ብይን፣ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 270002 ሰኔ 03 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ አመልካቾች ከተለያዩ አካላት እንዲቀርቡላቸው የጠየቋቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብ እና ከክሱ ጋር አያይዘው ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች እንደክስ አቀራረባቸው ለማስረዳት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው በአግባቡ ከለየ በኋላ በእያንዳንዱ ማስረጃ ላይ ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ትንታኔ በመስጠት አመልካቾች ዳኝነት በጠየቁበት ጉዳይ ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ ከሰጡት መልስ እና ካቀረቡት ማስረጃ ጋር ከፍሬነገር ክርክሩ ጋር አብሮ በማጣራት መርምሮ ተገቢ የሆነውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የዚህ ውሣኔ ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
- መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም